የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፹፰
አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 88
ADDIS ABABA 22nd August 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፶፪/፪ሺ፫

የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ ሀገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት /ማሻሻያ/ ደንብ . ገፅ ፮ሺ፩፻፲፪

## CONTENTS

Regulation No. 252/2011

Certain Rights and Privileges of Foreign Nationals of Ethiopian Origin to be Exercised in the Country of their Origin Council of Ministers (Amendment) Regulation ……………………………………………Page 6112

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፶፪/፪ሺ፫

## የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ ሀገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣውን ደንብ ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች በትውልድ ሀገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፸/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፲፯ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ ‹‹የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች በትውልድ ሀገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፪፻፶፪/፪ሺ፫›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ማሻሻያ

የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች በትውልድ ሀገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፩/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፭ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፭ ተተክቷል፡-

‹‹፭. የአገልግሎት ክፍያዎች

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፰ መሠረት የሚሰጠውን የትውልደ ኢትዮጵያ መታወቂያ ለማግኘት ፩፻ የአሜሪካን ዶላር ወይም በወቅቱ የምንዛሪ ተመን መሠረት ተመጣጣኝ የሆነ አመልካቹ የሚኖርበት ሀገር ገንዘብ ወይም በአገር ውስጥ ሲሆን ተመጣጣኝ የሆነ ብር የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል።

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 252/2011

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO AMEND THE REGULATION PROVIDING FOREIGN NATIONALS OF ETHIOPIAN ORIGIN WITH CERTAIN RIGHTS AND PRIVILEGES TO BE EXERCISED IN THE COUNTRY OF THEIR ORIGIN

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 17 of Certain Rights and Privileges of Foreign Nationals of Ethiopian Origin to be Exercised in their Country of Origin Proclamation No. 270/2002.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as "Certain Rights and Privileges of Foreign Nationals of Ethiopian Origin to be Exercised in the Country of their Origin Council of Ministers (Amendment) Regulation No. 252/2011".

### 2. Amendment

Article 5 of Certain Rights and Privileges of Foreign Nationals of Ethiopian Origin to be exercised in the Country of their Origin Council of Ministers Regulations No. 101/2004 is deleted and replaced by the following new Article 5:

‹‹5. **Service Fees**

1/ A fee of USD 100 or an equivalent sum of the local currency where the applicant resides or, if the applicant is in Ethiopia, an equivalent sum of Birr, on the basis of the prevailing exchange rate, shall be payable for the issuance of an Identification Card of Ethiopian Origin in accordance with Article 8 of the Proclamation.

ያንዱ ዋጋ Unit Price 2.30

ፖ.ሣ.ቁ. P.O. Box 80001

፪/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት የትውልደ ኢትዮጵያ መታወቂያ ለማሳደስ ፵ የአሜሪካን ዶላር ወይም በወቅቱ የምንዛሪ ተመን መሠረት ተመጣጣኝ የሆነ አመልካቹ የሚኖርበት ሀገር ገንዘብ ወይም በአገር ውስጥ ሲሆን ተመጣጣኝ የሆነ ብር የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፫/ የጠፋ ወይም የተበላሸ የትውልደ ኢትዮጵያ መታወቂያ ለመተካት ፷ የአሜሪካን ዶላር ወይም በወቅቱ የምንዛሪ ተመን መሠረት ተመጣጣኝ የሆነ አመልካቹ የሚኖርበት ሀገር ገንዘብ ወይም በአገር ውስጥ ሲሆን ተመጣጣኝ የሆነ ብር የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡ ሆኖም ለጠፋ መታወቂያ ምትክ ከመሰጠቱ በፊት አመልካቹ መታወቂያው ስለመጥፋቱ ለአካባቢው ፖሊስ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡"

፫. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

2/ A fee of USD 40 or an equivalent sum of the local currency where the applicant resides or, if the applicant is in Ethiopia, an equivalent sum of Birr, on the basis of the prevailing exchange rate, shall be payable for the renewal of an Identification Card of Ethiopian Origin in accordance with Article 4 of this Regulation.

3/ A fee of USD 60 or an equivalent sum of the local currency where the applicant resides or, if the applicant is in Ethiopia, an equivalent sum of Birr, on the basis of the prevailing exchange rate, shall be payable for the replacement of a lost or damaged Identification Card of Ethiopian Origin; provided, however, that the loss of the Identification Card shall be reported, by the applicant, to the local police prior to the issuance of a replacement."

3. **<u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of August, 2011.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት